# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**መስከረም 15 ቀን 2003 ዓ.ም.**

**መለስ በምሁራኖች እና በፖለቲካ ተንታኞች ተብጠለጠለ፤**

**በውጭ ሀገር ዜጎች ጭምር መለስ ዜናዊ በአሜሪካ ከፍተኛ ተቃውሞ ቀረበበት፤**

**መለስ በምስጢር ሱዳን ገብቶ እንደነበር ተጋለጠ፤**

**ወያኔ አዲስ ስርዓተ ትምህርት ቀርፆ አወጣ ከ2.5 ቢሊዮን ብር በላይ ለውጭ ሀገር ዜጎች ሰጠ፤**

ባለፈው ሳምንት የወያኔ ቡድን ሊቀመንበር እና የስራ አስፈፃሚ ሹመት በናዝሬት ከተማ ካደረገ ወዲህ የተደረገውን ሹም ሽረት በመቃወም ምሁራኖች በመለስ ላይ የሰላ ትችት እየሰነዘሩበት መሆኑ ታወቀ::

ለ19 ዓመታት በስልጣን ላይ የቆየው መለስ ዜናዊ እስከ ዛሬ ድረስ ከነበረው የበላይነቱ እጅግ በሰፋ መልኩ ስልጣኑን ከማጠናከሩም በላይ ብቸኛ አምባገነን ሆኖ የወጣበት ወቅት መሆኑን ምሁራኖቹ በይፋ እየተናገሩ ይገኛሉ::

ሰሞኑን በነባር የህወሀት ከፍተኛ ባለስልጣናት ላይ የቆረጣ ስልት ተጠቅሞ ካስወገደ ወዲህ ብቸኛ የምስራቅ አፍሪካ አምባገነን ግለሰብ መሆኑን አስመስክሮዋል ያሉት ምሁራኖቹ ከእንግዲህ ወዲያ በሀገሪቱ የአንድ ሰው ትእዛዝ ለመፈጸም ግድ የሚልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል ሲሉም ገልፀዋል::

ስማቸው እንዲገለፅ ያልፈለጉ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራኖች እንዳሉት ከሆነ መለስ ዜናዊ እንደ ደርጉ ሊቀመንበር መንግስቱ ኃይለማሪያም ብቸኛ አዛዥ ከመሆኑም በላይ የለየለት አምባገነን መሆኑን በሰሞኑ ተግባራዊ እንቅስቃሴው ያስመሰከረ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

እስከ ዛሬ ድረስ 19 ዓመታት እኔ ያልኩት ካልሆነ ሲል የነበረው መለስ አሁን በግላጭ ብቻውን ስልጣኑን ሁሉ ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሮ በመያዙ ሀገሪቱን ለድህነት ህዝቡን ለርሀብ የሚዳርግበት ወቅት ላይ ነን ሲሉም አስረድተዋል፡፡

የመለስ ቅርብ ሰው እና የወያኔ አበሉ ረዳት ፕሮፌሰር መድህኔ ታደሰ የተባለው ግለሰብም መለስ ብቸኛው አድራጊ ፈጣሪ ሆኖዋል ሲል መግለፁ ታውቆዋል፡፡ መድህኔ ታደሰ መለስ የቀድሞዎቹን የትግል አጋር የሚባሉትን ጠራርጎ በመጣል በአዳዲስ ታማኝ እና ታዛዥ ግለሰቦች በመተካት ስልጣኑን ከመቼውም ግዜ በላይ ያለ ተቀናቃኝ ማጠናከሩን ጨምሮ ገልፆዋል፡፡ አክሎም መለስ ከቀድሞ ጉዋደኞቹ ይልቅ ከተማ በቀል አዲስ የወያኔ ሹመኞች ጋር የጠበቀ ግንኙነት እና ወዳጅነት የፈጠረ ሲሆን ይህንንም ያደረገው በኢትዮጵያ ውስጥ የበላይነቱን ለማጠናከር ነው ሲልም ጨምሮ አስረድቶዋል፡፡

መድህኔ ታደሰ መለስን አምባገነን ሲልም ዘርጥጦ ያዋረደው ሲሆን ከእንግዲህ በኢትዮጵያ የአንድ ሰው አምባገነንነት የሰፈነበት ከመሆኑም በላይ ይቀናቀኑኛል ብሎ ያሰባቸውን የወያኔን ሰዎች አስወግዶ ከቅርብ ግዜ ወዲህ ብቅ ብቅ ያሉትን እንደነ ዶክተር ቲዎድሮስ አድህኖምን የመሳሰሉትን ጮሌዎች ሰብስቦ መያዙ አስገራሚ ነው ሲል አስረድቶዋል፡፡

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ለመገኘት ወደ አሜሪካ ኔውዮርክ ከተማ የተጉዋዘው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ድንገት ሳይታሰብ ወደ ሱዳን ገብቶ እንደነበር ተገለጠ፡፡

ለሶስት ቀናት በተደረገው ጉባዔ ላይ ለመገኘት ወደ ኔውዮርክ ያቀናው የወያኔው መሪ አምባገነኑ መለስ እግረ መንገዱን ወደ ሱዳን ጎራ ብሎ ከአልበሽር ጋር ውይይት አድርጎ የነበረ ሲሆን ውውይታቸው በቅርቡ ይከሄዳል ስለሚባለው የደቡብ ሱዳን የነጻነት ሪፍረንደም ጉዳይና ምእራባውን በሱዳን ላይ ስለሚያደርጉት ተጽእኖ ሳይሆን እንዳልቀረ ተገምቶአል፡፡ አልበሽር መለሰ በተባበሩት መንግሰታት ስብሰባ ላይ እነዘህን ጉዳዮቸ እንዲያቀርብለት የተማጸነ መ ሆኑ ታወቋል፡፡

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በኒውዮርክ ባዘጋጀው የመሪዎች ስብሰባ ላይ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊን ጨምሮ የ140 ሀገራት መሪዎች በጉባዔው ላይ ተሳታፊ እንደነበሩም ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

ጉባዔው  ልዩ ትኩረት አድረጎ የነበረው ድህነትን፤ ርሀብና በሽታዎችን ከዓለም በማስወገድ አጀንዳ ላይ ሲሆን ሊጠናቀቅ አምስት ዓመታት ብቻ የቀረውን የሚሊኒየሙ የልማት ግቦች እቅድ አካሄድ መገምገሙም ታውቆዋል::

በዚሁ ዓመታዊ የመንግስታቱ ጉባዔ ላይ መሪዎቹ የየሀገራቸውን እንቅስቃሴ የሚያሳይ ሪፖርቶችን ያቀረቡ ሲሆን መለስም እንደ ወትሮው ግዜ ሁሉ በዚሁ ቦታም ከፍተኛ ስራ እንደሰራ ሳያፍር ያለ አንዳች ይሉኝታ ገልፆዋል::

ተስፋ ሰጪ ብቻ ሳይሆን ትርጉም ያላቸው ለውጦችን አስመዝግበናል ወደፊት የራሳችንን እጣ ፈንታ ለመወሰንም በሙሉ አቅም እየተንቀሳቀስን እንገኛለን ያለው መለስ በዚህም ጉዞ በዓመት 11 በመቶ እድገት እያስመዘገብን ነው ሲል ገልፆ ለጋሽ ምዕራባውያን  ሀገራትን ብትሰጡን ስጡን ባትሰጡን እድሜ ለቻይና በሚል መልኩ  አስፈራርቶዋል::

በስብሰባው ላይ ከተገኘ በሁዋላ በዚያው በአሜሪካ  ኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲ  ንግግር እንዲያደርግ የተጠራ ቢሆንም የውጭ ሀገራት መምህራኖች ጭምር በፅኑ በመተቸት ከፍተኛ ተቃውሞ ማሰማታቸው ታውቆዋል::

በህዝብ እና በሀገር ብሎም በትውልድ ላይ ለ19 ዓመታት ሲጫወት እና ሲቀልድ የኖረው የወያኔ ቡድን እድገት እና ትራንስፎርሜሽን በሚል  አዲስ የስርዓተ የትምህርት ፖሊሲ ቀርፆ አውጥቶ እያሰራጨ መሆኑ ተጋለጠ::

ከህዝብ አፍ ላይ እየነጠቀ በበተነው ገንዘብ የውጭ ሀገር ምሁራን ናቸው ተብዬዎች አዲስ ስርዓተ ትምህርት  በምስጢር ቀርፀው ከማውጣታቸውም በተጨማሪ ወደየክልሉ እየተሰራጨ መሆኑን የትምህርት ሚኒስትር የውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ::

ከ2.5 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ተደረገበት የተባለው ይሄው ወያኔ ሰራሽ አዲስ የስርዓተ ትምህርት ቀረጻው በውጭ ሀገር ዜግነት ባላቸው ሰዎች ብቻ በምስጢር እንዲሰራ የተደረገ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮች ኢትዮጵያዊ ምሁራኖች ጭራሽ እንዳያውቁ ተደርጎ እንደተሰራ አጋልጠዋል::

የኢትዮጵያውያን ምሁራን  ከዚህ ቀደም ተቀርፆ ተግባራዊ የሆነውን  የወያኔ የትምህርት ፖሊሲ አጥብቀው ሲኮንኑ የነበረ ከመሆኑም በላይ     የሀገሪቱን ታሪክ እና የህዝቡን ባህል ጭራሽ በማያውቁ የውጭ ሀገራት ዜጎች ተቀረፀ የተባለው ይሄው አዲሱ ስርዓተ ትምህርት ዜጎችን ቁልቁል የሚቀብር ሀገርን ወደ ሁዋላ የሚጎትት ትውልድን የሚጎዳ ነው ሲሉ ጨምረው  አስረድተዋል:

የወያኔ ቡድን ህዝብን ለሌላ 20 ዓመታት እያዘናጋና እያታለለ ለመግዛት እንዲያመቸው በቅርቡ ባወጣው የትራንስፎርሜሽን እና እድገት የሚለውን ዕቅድ ይተገብራሉ ያላቸውን ካድሬዎች እየሾመ ሌሎቹን እያባረረ መሆኑን የደረሰን ጥቆማ ገለፀ::

አዲስ አበባን ጨምሮ በሌሎች ከተሞች ውስጥ ያሉ ካድሬዎች ላይ ሹም ሽረቱ ተጡዋጡፎ እንደሚገኝ የጠቆመው የደረሰን ጥቆማ በተለይ አዲስ አበባ በሁሉም ክፍለ ከተሞች ባሉ ወረዳዎች ውስጥ ምንጠራው ተቀጣጥሎ እንደሚገኝ አብራርቶዋል::

የእድገት እና ትራንስፎርሜሽኑ ዕቅድ ግቡን እንዲመታ ተፈላጊ ሰዎች በተፈላጊ ቦታ ይቀመጡ በሚል ከኩማ ደመቅሳ በተሰጠ ልዩ ትዕዛዝ መሰረት ሰሞኑን ቀድሞ ቀበሌ የነበረው በአሁኑ አጠራር የወረዳ ሊቀመንበሮች እና ስራ አስፈጻሚ በሚባሉት ላይ ተከታታይ ከስልጣን የማባረር እርምጃ እየተወሰደ ሲሆን በሌሎችም ከተሞች ተግባራዊ እየተደረገ ወያኔ እየታመሰ መሆኑንም ጨምሮ የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

በአዲስ አበባ ከተማ ካሉት ክፍለ ከተሞች ውስጥ ግንባር ቀደም ምንጠራ የተጀመረው በአራዳ ክፍለ ከተማ ነው ያለው የደረሰን ጥቆማ እሱን ተከትሎ በሌሎችም እርምጃው ጠንክሮ መቀጠሉን ገልፆዋል::

የወያኔው ቡድን እራሱ ሲያንቁዋሽሸው የነበረውን የኢትዮጵያ ሰንደቅአላማ አከብራለሁ ቢልም ለአራት ኪሎ ቤተ መንግስት ስልጣን በበቃ በማግስቱም ያለውን ከፍተኛ ጥላቻ በይፋ በመሪው መለስ ዜናዊ በኩል መግለፁ ይታወቃል::

በኢትዮጵያ ሰንደቅአላማ ላይ ስር የሰደደ ጥላቻ ያላቸው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ አና ቡድኑ በተደጋጋሚ ግዜ በየመድረኩ ጨርቅ እያሉ ሲያጣጥሉት ቢቆዩም ከሻዕቢያ ጋር ውጊያ በገጠሙበት ወቅት የኢትዮጵያን ህዝብ ለመለመን ሳይወዱ በግዳቸው አምነው ሰንደቅአላማውን ለመቀበል የተገደዱ መሆኑን የጠቆመው ዘገባ ከዚያን ግዜ ጀምሮ ህዝቡ ሰንደቅአላማው ፍቅር እንዳለው በማወቃቸው ዛሬ በየዓመቱ የባንዲራ ቀን በሚል ለይስሙላ እያከበሩት ይገኛሉ::

የባንዲራ ቀን በሚል በስታዲየም በተከበረበት እለት ህዝቡ እና የመንግስት ሰራተኛው ስራ ላይ እንዲሆን ተማሪው በትምህረት ላይ እንዲገኝ ተደርጎ ለወያኔ አሽቃበጭ እና አፈድፋጅ የሆኑት የወያኔ የሴቶች ሊግ አባል፤የወጣቶች ሊግ አባል ፤የፌዴራል ፖሊስ፤የመከላከያ አባሎች ብቻ በቦታው እንዲገኙ ና የመለስ እና ንብ ምስል ያለበት ቲሸርት እንዲለብሱ መደረጉ ዛሬም ሰንደቅአላማው ላይ ያላቸው ጥላቻ እንዳልተቀረፈ የሚያሳይ መሆኑን ከድርጊታቸው ለማረጋገጥ ተችሎዋል::

የባንዲራ ቀን በደማቅ ሁኔታ በብሔራዊ ደረጃ ተከብሮ ይውላል ተብሎ ሲለፈፍ እና ጡሩንባ ሲነፋ ሰንብቶ እንደተባለው ሳይሆን ቀርቶ በተሻፋፈነና በተድበሰበሰ መልኩ እንዲከበር የተደረገው በብሔራዊው ሰንደቅ አላማችን ላይ በወያኔ ማንአለብኝነት ለውጥ መደረጉን በርከታ ሕዝብ የሚቃወመው በመሆኑ ረብሻ ሊነሳ ይቸላል ከሚል ፍረሃት ሳይሆን አይቀርም በሚል ብዙዎች ግምታቸውን ይሰጣሉ:: ወያኔዎቸ ያደረጉት ቀድሞም ቢሆን የግብር ይውጣ ስራ በመሆኑ አደባባይ ላይ ሌላ አደባባይ በመሰየም በመስቀል አደባባይ የባንዲራ አደባባይ ተብሎ የመሰረት ድንጋይ ማኖራቸው ታውቆዋል::